የሕይወት ታሪኩ አሁን ሲነገር እንደሰማነው በዚህ ዓለም በኖረበት ዘመን ዕድሜውን ሙሉ በመማርና በማስተማር፤ በምርምርና በሥነጽሑፍ ዝግጅት ያሳለፈው ወንድማችን በትውልዳችን ታሪክ ውስጥ ቋሚ መታሰቢያ ሊቆምለት የሚገባ የተከበረ ኢትዮጵያዊ ነው። "ዶክተር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ"

በተማሪነቱም ሆነ በተመራማሪነት፣ በመምህርነቱም ሆነ በደራሲነቱ፣ የደከመውና ከፍተኛ ጥረት ያደረገው፣ በሚወዳት አገሩ በታላቋ ኢተዮጵያችን ጥንታዊ ሥልጣኔና ታሪክ ላይ የተመሠረተ ስለሆነ፣ ፍሪያማ በሆኑት አገልግሎቶቹ የኛና ከኛም የቀጠለው ትውልድ ሲጠቀምበትና ሲያስታውሰው እንደሚኖር አንጠራጠርም።

እኔ በበኩሌ በቤተሰብነት ካለኝ ግንኙነት ሌላ፣ በተለይ ስለ ዶክተር ሥርግው ጥናትና ምርምር ለማወቅና ለመረዳት የቻልኩት፣ የዛሬ አርባ-ሰባት ዓመት በነሐሴ ፲፱፻፶፯ ዓ. ም. በዚሁ በጀርመን አገር ኮለኝ በተባለው ከተማ ላይ በመላ አውሮፓ ለሚገኙት ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ስብሰባ ላይ ነው። ይህንንም ለመጀመሪያ ጊዜ የተደረገው በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ስብሰባ፣ ያዘጋጀውና በሊቀመንበርነት የመራው በዚያን ጊዜ በእንግሊዝ አገር ያለው የኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ማህበር ፕሬዝደንት የሆነው የዶክተር ሥርግው ታናሽ ወንድም ልጅ ስብሐት ሐብለ ሥላሴ ነበር።

ዶክተር ሥርግው በዚያን ጊዜ በግሪክ አገር በአቴና ዩኒቨርስቲ በቴዎሎጂና በጥንታዊ ታሪክ ተመርቆ ለፒ.ኤች.ዲው ወደ ቦን ዩነቨርስቲ ለመዛወር የሚዘጋጅበት ግዜ ሲሆን እኔም በፓሪስ የጋዜጠኝነት ሞያ የማጠናበት ዘመን ነበር።

በዚህ በኮሎኝ ስበሰባ ላይ ስለ ዶክተር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ በአእምሮዬ ተቀርጾ የሚኖረው ትልቁ ትዝታዬ፣ ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበረውን የኢትዮጵያችንን የንግሥተ ሳባንና የሰሎሞንን ግንኙነት፣ ከዚያም እስከ ቀዳማዊ ምኒልክ ድረስ ያለውን ታሪክ እንድናውቅ ወንድማችን የሰጠንን ትምህርት ነው።

ብዙዎቻችን የልጅነት ሕይወታችንን እንደምናስታውሰው ይህንን የአገራችንን መሠረታዊ ታሪክ ልብወለድ እያረጉ በማሾፍ የግብር ይውጣ የሚያስተምሩን የውጭ አገር ተወላጅ መምህራኖች ስለሆኑ ለመጀመሪያ ጊዜ በተጣራ አማርኛና በጣፈጠ አቀራረብ ትክክለኛውን ታሪካችንን ያቀረበልንን ወንድማችንን ዶክተር ሥርግው ሐብለ ሥላሴን በአክብሮትና በአድናቆት ስናስታውሰው እንኖራለን።

የዚህ የኮሎኝ ስብሰባ ከተካሄደ ከአምስት ዓመታት በኋላ ሁላችንም ወደ አገራችን ተመልሰን በየሞያችን በመንግሥት ሥራ ላይ በምንገኝበት ጊዜ በማስታወቂያ ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ራዲዮ ስለ አገራችን ጥንታዊ ታሪክና ሥልጣኔ ሕዝቡን ለማስተማር አዲስ ፕሮግራም ስንከፍት የመጀመሪያው መምህራችን እንዲሆን የተመረጠው ወንድማችን ዶክተር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ ነበር። ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ የተቋቋመው የራዲዮ ፕሮግራም እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በሚያዝያ ፲፱፻፷፪ ዓ. ም. በተመረቀበት ዕለት ዶክተር ሥርግው ሐብለሥላሴ ካደረገው የመክፈቻ ንግግር አንዱን ፓራግራፍ ልጠቅስላችሁ እወዳለሁ።

"...እኛ ኢትዮጵያውያኖች ምን ዓይነት ሕዝቦች እንደሆንን ምን ዓይነት ጥንታዊ ታሪክና ሥልጣኔ ይዘን እንደመጣን ምን ዓይነት ባሕልና ጠባይ እንዳለን በምን ዓይነት ጉዞ መከራዎችንና ፈተናዎችን እየተቀበልን አለንበት ዘመን ለመድረስ እንደቻልን መሠረታዊ ታሪካችንን ደህና አድርገን ካላወቅን እንዲሁ በደፈናው የሶስት ሺህ ዘመን ሥልጣኔና ዝና አለን እያልን ብንኮራ የሚያከብረን ሆነ በቁምነገር የሚያዳምጠን አናገኝም። ለጥንታዊው ታሪካችንና ለሚደነቀው ሥርዓታችን፣ ባለቤቶቹ እኛው ብቻ ስለሆንን የባዕድ ተወላጅ ሊቃውንቶች አጣርተው ያስተምሩናል። አብራርተው ያቀርቡልናል ብለን መጠበቅ አይገባንም። መማሩና መመራመሩ የኛው የራሳችን ተግባርና ግዳጅ መሆኑን በቅድሚያ መገንዘብ አለብን። የራሱን ታሪክ ሳያውቅ በሌሎች አገሮች ታሪክ የጠለቀ ምርምርና ጥናት አከናውኖ የተመረቀም ሆነ የተደነቀ ኢትዮጵያዊነቱን የተሟላ ሊያደርግለት አይችልም።"

ሲል ዶክተር ሥርግው ሐብለሥላሴ የገለጸው አስተያየት <u>በትምህርት ዓለም ውስጥ የሚገኙት ሁሉ</u> ስለ ኢትዮጵያ መሠረታዊ ታሪክ ለማወቅ እንዲችሉ የሚያተጋ ማሳሳቢያ ነው በማለት፣ በኢትዮጵያ ራድዮ አድማጮች ብቻ ሳይሆን በንጉሡ ነጋሥቱ መንግሥት ባለሥልጣኖችም ዘንድ ከፍተኛ ግምት ተሰጥቶት ነበር።

ዶክተር ሥርግው እንደተናገረው በተለይ የኛ ትውልድ ከአገራችን ጉዳይ ይልቅ ጠንቅቀን የምናውቀው የውጭውን ዓለም ታሪክ በመሆኑ ብዙዎቻችን እንኳ የሚያረካ መልስ ለመስጠት ችሎታው አልነበረንም። ወላጆቻችን ለሕይወት ኑሮአችን መቋቋሚያ እንደሚያዘጋጁልን ኑዛዜ ሊቃውንቶቻችንም የተማሩበትን ሰነዶች በድርሰት አሰናድተውልን ባለመሄዳቸው በታሪክ ረገድ ያለው የኢትዮጵያውያን ጥማት በቶሎ ሊወገድ የሚቻል አልሆነም። ወንድማችን ዶክተር ሥርግውም በማስተማርና በመመራመር ከዚያም በላይ ሥነ ጽሑፎችን ለማዳበር መላ ሕይወቱን የመደበው ይህንን በታሪክ ሥልጠና ረገድ በኢትዮጵያውያን ላይ ለደረሰው ችግር በማሰብና በመጨነቅ መሆኑን ማንም ሰው ለመገንዘብ አያዳግተውም።

ዶክተር ሥርግው እንደአሰበውና እንደተመኘው ሙሉ ጤናና የዕድሜ ፀጋ አግኞቶ ያሰበውን ሁሉ ለመፈጸም ባይችልም የፈጣሪያችን ጥሪ እስከመጣለት ድረስ የበኩሉን ድርሻ በሚገባ ያበረከተና እስከመጨረሻይቱ ዕለት ድረስ ባለሚቋረጥ የታገለ ስለሆነ ለጥንካሬውና ለዕምነቱ ለዓላማውና ለፈረያማው አገልግሎቱ አክብሮታችንና አድናቆታችን ምንጊዜም አይለየውም።

ለአስተዋይነት ከተመቸው መልካም ጠባዩ ጋር ቅንነትና ታማኝነት ሳይለየው በኖረበት ዘመን የአምስት ልጆች አባት ሆኖ ለቁምነገር በማድረስ የልጅ ልጆች ለማፍራት የቻለ ስለሆነ ለሚወዳት አገሩ ለኢትዮጵያ ካበረከተው የታሪክና የሥነጽሑፍ አገልግሎት ጋር ሲደመር ዶክተር ሥርግው ምንጊዜም ሲታወስ የሚኖርበትን ዋና ዋና መታሰቢያዎችን መሥርቶ እናገኘዋለን።

መሬት ነህና ወደ መሬት ትመለሳለህ እንደተባለው ወንድማችን ሥጋው አፈር በሚለብስበት በዛሬው ዕለት የምንሰናበተው በከፍተኛ ሀዘን ቢሆንም ዶክተር ሥርግው በፈጸማቸው ከፍተኛ ተግባሮች እየተጽናናን አምላክ ነፍሱን በሠላም እንዲቀበልልን እንፀልያለን።

አምባሳዶር ዘውዴ ረታ
ጥር ፯ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ. ም.
ሙኒክ